# አንድነትና መኢአድ በመጪው ምርጫ ያላቸው ስፍራ

ክፍል ሶስት

ኢብሳ ነመራ

12-24-14

በክፍል ሁለት ፅሁፍ አንድነት ምርጫ ቦርድ ያቀረበለትን የአመራር ችግሩን እንዲያፀዳ የሚጠይቅ ማሳሰቢያ በበጎ ጎን ከመቀበል ይልግ "በምርጫ ቦርድ ደባ አንድነት አይደናገጥም" በሚል ፉከራ ቀመስ ርዕስ ያወጣውን መግለጫና አንድምታዎቹን መመልከት ጀምረን ነበር ያቋረጥነው። በዚህ ክፍል ሶስት ፅሁፍ ካቆምንበት እንቀጥላለን።

ኢትዮጵያን ዳግም ሃገር ልትሆን በማትችልበት ሁኔታ የማተራመስ ህልም ይዞ ለዚህ ማስፈፀሚያ ያግዘኛል ያለውን የትርምስ ስትራቴጂ የነደፈው የኤርትራው ሻአቢያ "የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ነን" የሚሉ እንደግንቦት 7 ያሉ ቡድኖችን ተላላኪዎቹ ማድረጉን የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃል። ግንቦት 7ን የመሳሰሉ የሻአቢያ ተላላኪዎች ደግሞ በሃገር ውስጥ ህጋዊ ሆነው የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ በአመራርነት የተሰገሰጉ የሁከትና ግርግር፣ የሽብር ጉዳይ አስፈፃሚዎች እንዳሏቸው አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ ይረዳል። "ለአመፅ ተነሳ" ከሚል ጥሪ ጀርባ ሁሌም ሻአቢያ መኖሩን ይጠረጥራል። እናም እንደ ዋዛ 'ሆ' በሎ ለአመፅ አደባባይ አይወጣም። ከዚህ ቀደመ ህጋዊ ሆነው በሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ሽፋን የተለያዩ አጋጣሚዎችን መነሻ በማደረግ ሊለኮሱ የተፈለጉ አመፆች አነደተፈለገው ወደህዝባዊ አመፅነት ሳይለወጡ የጥቂት ሰዎች ጫጫታና ድንጋይ ውርወራ ሆነው የከሰሙት በዚህ ምክንያት መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን ኢትዮጵያ ሰርቶ የመኖር ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ሁሉ ስራ ላይ መሰማራት የሚያስችል ሰፊ ዕድል ተመቻችቶባታል። ይህን ያደረገው መንግስት ነው። መስራት የሚፈለጉ ዜጎች ሁሉ ያዋጣኛል ብለው ባመኑበት የንግድ፣ የአገለግሎትና የማምረት ሳራ ላይ በግልም ሆነ በማህበር ተደራጅተው እንዲሰሩ የሚያስቸሉ ሁኔታዎች ተዘጋጅተዋል። የብድር፣ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ በመንግስት ይዘጋጃል። እንዲሁም

የገበያ ትስስር ይፈጠርላቸዋል። በሃገሪቱ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለው የኮንስትራክሽን፣ የአገልግሎትና የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪም ለበርካታ ወጣቶች ሰፊ የስራ እድል ፈጥሯል። እስካሁን በዚህ እድል ተጠቃሚ መሆን ላልቻሉትም ቢሆን ስራ የማግኘት ተስፋ ፈጥሯል።

አንድነት "በምርጫ ቦርድ ደባ አንድነት አይደናገጥም" በሚል ለሻአቢያ ተላላኪ ሚዲያዎች ፈጅታ ያዘጋጀው መግለጫ "በአሁኑ ሰአት ህዝቡ በኑሮ ውድነትና በስራ እጦት ከመሰቃየቱም በላይ ሙሰና ሰፈቷል። የመልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት ፈፅሞ ጠፍቷል።" ብሏል። አንድነት በሃገሪቱ የስርአት ለውጥ የሚሻ ቀውስ አለ ባይ ነው። እርግጥ ነው ባለፉ አምስት ስድስት አመታት የዋጋ ነረት ተከስቷል። ይህ የዋጋ ንረቱ ከሁለት ዓመት በፊት 40 በመቶ ደርሶ እንደነበረም እናስታውሳለን። ይህን የህዝቡ የኑሮ ሁኔታ ላይ ጫን ያለ ተፅእኖ ፈጥሮ የነበረ የዋጋ ንረት መንግስት እነደችግር ልዩ ትኩረት ሰጥቶት ነበር የተንቀሳቀሰው።

የዋጋ ንረቱ የተለያዩ መንስኤዎቸ ነበሩት። እነዚህም በሃገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ የተመዘገበው ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ያስከተለው ተጨማሪ የገበያ ፍላጎት፣ በውስጥ ለውስጥ ስምምነት የተፈጠረው የገበያ ዋጋን የማዘዝ አቅም ያለው የነጋዴዎች ሞኖፖሊ፣ ዓለምን የመታው የገንዘብ ቀውስ፣ እንዲሁም መንግስት የትላልቅ ፕሮጀክቶችን ወጪ ለመሸፈን የተከተለው ገንዘብ ከብሄራዊ ባንክ የመበደር አካሄዶች ናቸው። መንግስት እነዚህን የዋጋ ንረት መንስኤዎች ከለየና ለህዝብ ካሳወቀ በኋላ ችግሩን መከላከል ወደሚየስችሉ እርምጃዎች ተሸጋገረ።

የኢኮኖሚ እድገት የፈጠረው ተጨማሪ የገበያ ፍላጎት ያስከተለውን የዋጋ ንረት ለመከላከል ቀዳሚው እርምጃ የኢኮኖሚውን እድገት በማስቀጠል እያደገ የሚሄደውን የገበያ ፍላጎት ማሟላት ነው። "እድገቱ የፈጠረውን የዋጋ ንረት ለማስተካከል የኢኮኖሚ እድገታችሁን ገታ አድርጉ" የሚል የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት አስተያየት ቢቀርብለትም ይህን ባለመቀበል የኢኮኖሚ እድገቱን በማስቀጠል አቋሙ ፀንቷል። ይህ እድገቱን የማስቀጠል እርምጃ አሁንም ገና በሂደት ላይ ቢሆንም ዋጋን በማረጋጋት ረገድ እስካሁን ተጨባጭ

ለውጥ ማሳየት አስችሏል። ለዚህ አስረጂነት በሲሚንቶ ዋጋ ላይ የታየውን እጅግ ከፍተኛ መሻሻል መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ የዋጋ ንረቱ ዋነኛ ተጎጂ የሆነው የመንግስት ሰራተኞች ደሞዝ ላይ ማሻሻያ አደረገ። ከዚሁ ጋር በማማያያዝ በነጋዴዎች ስውር መመሳጠር የተፈጠረውን ሰውሰራሽ የሸቀጦች አቅርቦት እጥረትና ዋጋን በመስማማት የመወሰን አካሄድ ለመከላከል የምግብ ዘይት፣ ሰኳር፣ የስንዴ ዱቄትና ዳቦ የመሳሰሉ መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የስርጭትና የዋጋ ቁጥጥር ስርአት ዘረጋ። በዚህ ምክንያት እነዚህ ሸቀጦች ላይ ላለፉ አራት ተከታታይ አመታት የዋጋ ጭማሪ አልታየም ማለት ይቻላል። መንግስት የሚያከናውናቸውን የኢኮኖሚ እድገቱን የሚያፋጠኑ የመሰረተ ልማትና ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶች ወጪን ለመሸፈን ከብሄራዊ ባንክ የሚበደረበት አካሄድም ለዋጋ ንረቱ መንስኤ በመሆኑ ይህን ትቶ በኢኮኖሚ ውስጥ ከሚንቀሳቀስ ገንዘብ የሚበደረበትን የፖሊሲ ማሻሻያ አደረገ።

እነዚህ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የዋጋ ንረት ማረጋጊያ እርምጃዎች የዋጋ ንረቱን እጅግ በሚያስገርም ደረጃና ፍጥነት ማስተካከል አስቻሉ። የእርምጃዎቹን መወሰድ ተከተሎ 40 በመቶ ደርሶ የነበረው የዋጋ ነረት ወደ አንድ አሃዝ ዝቅ አለ። ይህ ባለ አንድ አሃዝ የዋጋ ነረት (አሁን ባለው ሁኔታ ከ6 በመቶ በታች ወርዷል) የኢኮኖሚ እድገቱን የሚያነቃቃና ተገቢ ነው።

የዋጋ ንረቱ ሊሆን የሚገባው አነስተኛ ደረጃ ላይ ቢደርስም ቀደም ሲል ተሰቅሎ የነበረው ዋጋ ተፅአኖውን ማድረስ ያላቋረጠበት ሁኔታ መፈፀሩ ግን አይካድም። ይህን የዋጋ ጫና ለማቃለል የገቢያቸው መሻሻል በመንግስት ውሳኔ ላይ ጥገኛ ለሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ከ29 እስከ 40 በመቶ የሚደርስ የደሞዝ ማስተካከያ ተደረገ፤ ከሶስት ወራት በፊት።

በዚህ ምክንያት አሁን አንድነት እንደሚያወራው ከህዝቡ አቅም በላይ የሆነ ፈታኝ የዋጋ ንረት ችግር የለም። እርግጥ በሃገሪቱ አሁንም ድህነት በመኖሩ ሁሉም ዜጋ አምራችና ፍላጎቱን ያሟላ እንዲሆን ለማስቻል የኢኮኖሚ እድገቱን በማስቀጠል እርምጃ እየገፋበት ነው።

አንድነት በመግለጫው "ዜጎች በስራ አጥነት እየተሰቃዩ ነው" ብሏል። እርግጥ ነው በሃገሪቱ ለዘመናት ስር ሰዶ ከነበረውና ዘመን ተሻግሮ ወደዚህኛው ትውልድ ከመጣው ድህነት የተወረሰ የስራ አጥነት ችግር አሁንም ሙሉ በሙሉ የተወገደበት ደረጃ ላይ አለተደረሰም። ያም ሆኖ ባለፉ አንድ አስርት ዓመታት ግን የስራ አጥነት ችግር በሃገሪቱ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የሚቃለልበት እርምጃዎች ተወስደዋል።

አሁን ዜጎች የመነሻ ካፒታል ባይኖራቸውም እነደእውቀትና ጉልበታቸው ደረጃ በሚፈጥሩት ማናቸውም የስራ መስክ ላይ በግልና በማህበር በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ተደራጅተው ስራ ላይ መሰማራት የሚያስችላቸው ሁኔታ ተዘጋጅቷል። መስራት ለሚፈለጉና ለተደራጁ ስራአጥ ዜጎቸ መንግስት የገንዘብ ብድር፣ የመስሪያ ቦታ፣ የሙያና ሌሎች ድጋፎች የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቷል። ባለፉ አራት አመታት ብቻ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ለ6 ሚሊየን ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል። የኢኮኖሚው እድገትም በተለይ ከፍተኛ የሰው ሃይል የሚፈልገውና በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት ያደገው የኮንስትራክሽን ዘረፉም በመላው ሃገሪቱ በሚሊየን ለሚቆጠሩ ዜጎቸ የስራ እድል ፈጥረዋል።

በገጠር ያለውን ከእርሻ መሬት አለቦነት የመነጨ ስራ አጥነት ለማቃለል የሚያስችል ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል። በተለይ በመላው ሃገሪቱ በስፋት ከሚካሄደው የተፋሰስ ልማትና የአካባቢ እንክብካቤ ስራ ጋር በተያያዘ የገጠር ስራ አጦች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል። በተፋሰስ ልማት እንዲያገግሙ በተደረጉና አረንጓዴ በለበሱ ተራራማ መሬቶች ላይ ስራ አጥ ወጣቶቸ ንብ በማነብና በለማው መሬት ላይ የሚበቅለውን ሳር በመኖነት በመጠቀም ከብት የማደለብ ስራ ላይ መሰማራት የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተለይ በትላልቅ የሃገሪቱ ከተሞች አቅራቢያ የተሰፋፉት የአበባና የፍራፍሬ ልማት ኢንቨስትመንቶች በለበርካታ የገጠር ስራ አጦች የስራ እድል ፈጥረዋል። በተለይ ሴቶች በስፋት የዚህ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል።

የመልካም አስተዳደር ችግር መኖሩም እወነት ነው። በሃገሪቱ የመልካም አስተዳደር ላይ ያለው ችግር በመንግስት ስራና ሃላፊነት ላይ ካለ የተዛባ አመለካከት የመነጨ ነው። ይህን አመለካከት የኢፌዴሪ መንግስት ወይም ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አይደለም የፈጠረው።

ከፊውዳፋላዊና ወታደራዊ ስርአቶች እየተንከባለለ እዚህ የደረሰ አሁን ባለውም ስርአት ተፅእኖውን እያሳረፈ ያለ ችግር ነው። በዘውዳዊና ወታደራዊ ደርግ የመንግስት ስርአቶች የመንግስት ሰራተኞችና ተሿሚዎች የህዝብ አገልገሎት ሰጪዎች ተደረገው አይወሰዱም ነበር። ከዚህ ይልቅ በህዝቡ ላይ ያሻቸውን የሚወስኑና የሚያዙ ገዚዎችና የበላዮች እንደሆኑ ነበር የሚታሰቡት። ይህ የአገልጋይነት ሰሜት አለመኖር ሙስናንም የሚቀበል የስራ ባህል ፈጥሯል።

በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደርን ማስፈንና ሙስናን ለማስወገድ በቅድሚያ የመንግስት ስራንና ስልጣንን በተመለከተ ያለው ስር የሰደደው አመለካከት መቀየር አለበት። በዚህ ላይ ያለው የአመለካከት ለውጥ ስራ እንደማንኛውም ስር የሰደደና ባህል የሆነ አመለካት ላይ ለውጥ የማምጣት ስራ ሰፊ ጥረትንና የአንድ ትውልድ እድሜን ያህል ግዜን የሚጠይቅ ነው። መንግስት ይህን ታሳቢ በማድረግ የመልካም አሰተዳደር ችግር የኢኮኖሚ እድገቱን ለአደጋ የሚዳርግ አስከፊ ችግር መሆኑን፣ ሙስና ከኢኮኖሚውም እድገት አልፎ ለስርአቱም አደጋ መሆኑን በይፋ ተናግሯል።

በመናገር አልተገደበም። መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ህዝባዊ እንቅስቃሴ የመፍጠር ዘመቻ አወጆ ይህን በመተግባር ላይ ይገኛል። ሙስናን ለመዋጋትና ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ ለመፍጠረ የስነምግባርና የጸረሙስና ኮምሽን በፌደራልና በክልል ደረጃ ተቋቁሞ ሰፊ የአመለካከት ለውጥና የቁጥጥር ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

በቀደሙት ስርአቶች ቢሆን “ለሰማይ ለምድር የከበዱ” ተበለው አይነኬ ተደርገው ይወሰዱ የነበሩ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ጭምር በሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል። ጥፋተኝነታቸው በማስረጃ ተረጋግጦ ቅጣት ተወስኖባቸው ማረሚያ ቤት ወርደዋል። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በይፋ ሙስናን የሚያንቆለጳጵስ ሰው የለም። ጉቦ የባለስልጣንነት ምግባርና ወግ ተደርጎ አይወሰድም። ድርጊቱ ፀያፍ መሆኑን ሁሉም ተገንዝቧል። የመንግስት ሰራተኛውም የህዝብ አገልጋይ መሆናቸውነ ተገንዝበዋል።

ይሁን እንጂ እነደሌባ ተደብቆ የሚሞስኑ፣ ተደብቀው በአግባቡ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ሃላፊዎችና ሰራተኞች አሉ። ሙሉ በሙሉ ሙስናን ማስወገድና መልካም

አስተዳደርን ማስፈን ባይቻልም መሰረተቱ ግን ተጥሏል። ይህ በራሱ ትልቅ ስኬት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ ማንም ሊረዳው የሚችል እውነታ ነው።

“የጠራ ድርጅታዊ ቁመናና ከውዝግብ የፀዳ አመራር ይዘህ ወደምርጫ ግባ” የሚል ጥያቄ የቀረበለት አንድነት ፓርቲ ከላይ የተገለፁትን በነባራዊነት የሌሉ፣ በአመራሮቹ ጭንቅላት ውስጥ ያሉና ውዥንብር መፍጠር ሲፈልጉ በዘፈቀደ የሚለቋቸውን መሰረተ ቢስ ወሬዎች ከዘባረቀ በኋላ ወደገገርው ፓርቲ ኢ.ህአዴግ ተሸጋገረ። አንድነት ባወጣው ፎካሪ መግለጫው “ኢ.ህአዴግ በፍርሃትና በጭንቀት እየራደ ነው። ምረጡኝ በሎ ሕዝብ ፊት ለመቅረብ የሚያስችለው የፖለቲካና የሞራል ሃይል የለውም። አሁን የቀረው ማሸነፊያ መንገድ አንድነት ፓርቲን በመዝጋት ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ አንድነት ላይ ዘመቻ ከፍቷል።” ብሏል።

ይህ የአንድነት መግለጫ ላይ የሰፈረ ሃሳብ አንድነት እነደፓርቲ ራሱን እንደማያውቅ ያሳያል። “የሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ” እንዲሉ አንድነት የኢ.ትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በምን አኳኋን እንደሚመለከቱት ፈፅሞ እንደማያውቅ ያመለክታል። አንድነት በዚሁ ርዕስ በቀረበው ክፍል ሁለት ፅሁፍ ላይ አመራሮቹ የተናገሩትን በዋቢነት ጠቅሰን እንደተመለከትነው በአሳፋሪ የአመራር ሹክቻና ውዝግብ የተጠመደ፣ በውጭ የሚኖሩ የሻአቢያ ተላላኪዎችን የገንዘብ እርጥባን በመጎምጀት የቆሸሸ፣ የራሳቸው ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች ገንዘብ እያሳዩ እነደፈለጉ የሚያሾሩትና የሚያዙት አቋም የሌለው ደካማ ፓርቲ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ፓርቲው ሲቋቋምም የተመሰረተበት የፖለቲካ አቋም በአዲሲቱ ኢ.ትዮጲያ ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለው ሞቶ የበሰበሰ አቋም ነው። አንድነት “የግለሰብ እንጂ የቡድን መብት የለም” የሚል መርህ ላይ መመሰረቱን ይናገራል። ይህን አቋም መነሻ በማድረግ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት ጥያቄን ይቃወማል። አንድነት የቡድን መብት የለም የሚለውን አቋም የያዘው “የብሄሮችንና ብሄረሰቦችን መብትና ነፃነት ጥያቄ ዋጋ ማሳጣት እችላለሁ” በሚል እሳቤ ነው። ለአንድነት በኢ.ትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሉም። የብሄሮችና ብሄረሰቦች መብትና ነፃነት የሚባል ጥያቄም የለም።

እውነታው ግን አንድነት በአቋም ደረጃ ከያዘው የተለየ ነው። በኢትዮጵያ ለአንድ መቶ አመታት ያህል በብሄራዊ ማንነታቸው እንደ ማህበረሰብ ተለይተው ለአሰከፊ ጭቆና የተዳረጉ በቋንቋቸው እንዳይናገሩ፣ ባህላቸውን እንዳያሳድጉ እውነተኛ ታሪካቸው እንዳይገለፅ የተደረጉ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች አሉ። የእነዚህን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነቶችን የግለሰብ መብትና ነፃነት በማክበር ብቻ መመለስ አይቻልም።

ብሄራዊ መብቶቻቸው በባህሪያቸው ማህበራዊና እንደቡድን መብት ተቋማዊ በሆነ አካሄድ ብቻ ሊመለሱ የሚችሉ ናቸው። ፍርድ ቤት፣ የመንግስት ተቋማት . . . በአንድ ቋንቋ እንዲሰሩ ተደርጎ ሲያበቃ፣ "ሁሉም ዜጎች እንደግለሰብ በፈለጉት ቋንቋ የመጠቀም መብት አላቸው" በማለት በቋነቋቸው የመጠቀመ መብታቸውን ማረጋገጥ አይቻልም። ሰዎች እንደ ግለሰብ ያላቸውን በሚችሉት ቋንቋ የመናገረ መብት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ተመሳሳይ ቋንቋ ተናጋሪ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በሚኖሩበት አካባቢ በብሄራዊ ቋነቋ የሚሰሩ ተቋማት መኖር ይኖርባቸዋል። ይህ ደግሞ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ተግባራዊ ማድረግ ይሻል።

የአንድነት አመራሮች ብሄራዊ መብትና ነፃነትን እንደቡድን መብት መቀበል ያልፈለጉት የአንድ ብሄር የበላይነት ላይ የተመሰረተ መገለጫ ያለው አሃዳዊ የመንግስት ስርአት የመመስረት ራዕይ ስላላቸው ነው። በሌላ አነጋገር የቀደመውን አሃዳዊ ስርአት የመመለስ ፍላጎት ስላላቸው ነው። ለዚህ ራእይ ተግባራዊነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አወቃቀር በብሄራዊ ማንነት ላይ ሳይሆን በመልከዓ ምድር - በወንዝ፣ በሸለቆ፣ በተራራ . . ላይ መመስረት አለበት የሚል የፖለቲካ ፕሮግራም የዟል። አንድነት ይህን አቋም የመያዝ ህገመንግስታዊ መብት ያለው መሆኑን እገነዘባለሁ። ልተች የምፈለገው አሁን ባለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ያለውን ተቀባይነትና አዛላቂነት ነው።

የአንድነት እንደአቋም የያዘው በመልከአምድር ላይ የተመሰረተ የአስተዳደር አወቃቀር ከዚህ በፊት ተሞክሯል። በዘውዳዊው ስርአት ጠቅላይ ግዛትና በደርግ ክፍለ ሃገርና አስተዳደር ክልል። ይህ መልከአምድራዊ አወቃቀር አንድን ብሄር ሁለትና ከዚያ በላይ ቦታ በመሸንሸን፣ ሁለትና ከዚያ በላይ ብሄሮችን በአንድ ላይ በመጨፍለቅ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር _ በመረጡት ተወካይ የመተዳደር፣ በቋንቋቸው የመስራት፣

ባህላቸውን የማሳደግ፣ ታሪካቸውን የመንከባከብ መብታቸውን ተግባራዊ ከማድረግ ይገድባቸዋል። ይህ የከፋፍለህ ግዛ ስልት ብሄሮችንና ብሄረሰቦችን በመሸንሸን የመብትና ነፃነት ጥያቄ ማንሳትና መተግበር የማይችሉ ህዳጣንና ደካማ ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ የአንድነት አቋም "የሃገር አንድነት" በሚል ሽፋን፣ መብትና ነፃነት፣ ጥቅምና ፍላጎት ያለውን ህዝብ - ሰውን ወደጎን በመግፋት ለገዢዎች መፈንጫ የሚሆን የወሰን አንድነት ያለው ግዛት ከመፈጠር ፍላጎት የመነጨ ነው። ይህ አንድነት ሊያመጣው የሚፈለገው የወሰን አንድነት ላይ ብቻ የተመሰረተ አሃዳዊ ስርአት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ተሞክሮ ከፍተኛ የህይወት መስዋእትነትን በጠየቀ መራራ የብሄራዊ ነፃነት ትግል የተወገደና የተቀበረ ነው። ይህ አሃዳዊ ስርአት የመመሰረት አመለካከት አሁን በስብሷል። አንድነትና መሰሎቹ ጋር ግን አሁንም አለ፣ እነደበሰበሰ።

ይህ ብስብስ አመለካከት በኢፌዴሪ ህገመንግስት የሉአላዊት ኢትዮጵያ ስልጣን ባለቤት በሆኑና ተከባብረው ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በእኩለነት ለመኖር በተስማሙ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዘንድ ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም። እናም አንድነት በዚህ የፖለቲካ አቋሙ "ኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ ውክልና ስልጣን ይረከባል" ብሎ ማሰብ ጉም እንደመዝገን ይቆጠራል። ይህ ደግሞ አንድነት ለህዝብ ይዞ የሚቀረበው ስልጣን ሊያሰጥ የሚያስችል ምንም አማራጭ የሌለው ሙት ፓርቲ መሆኑን ያመለክታል። እናም በጭንቀት በመራወጥ ላይ ነው፤ ከምርጫ ውጭ ወደስልጣን ሊያመጣ የሚችል መንገድ የኖር እንደሆነ ወደውጭና ውስጥ አያማተረ በመቁለጭለጭ ላይ ያለ ፓርቲ ነው። የፎከረና የጮኸ ሁሉ ስልጣን ሊያሰጠው የመችል እየመሰለው በመነከራተት ላይ ያለ ፓርቲ ነው።

አንድነት የያዘው ለብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት እውቅና የነፈገ አቋም ህዝብ ፊት ለመቅረብ የሚያስችል የሞራል አቅም እንዳይኖረው አድርጎታል። አንድነት ከአዲስ አበባና ከጥቂት ትላልቅ የሃገሪቱ ከተሞች ውጭ በኦሮሚያ፣ በኢትዮጵያ ሶማሌ፣ በአፋር፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ በሲዳማ፣ ወላይታ … ብሄሮች ፊት ማንነቱን መናገር የማይችል ሙት ፓርቲ ነው። አንድነት አዲሰ አበባ ውስጥ ሲጮህ ነው ትልቀ

የሚመስለው። ኢትዮጵያ ውስጥ መሎሎህ የሚያስችል ስፍራም ድምፅም የለውም። ሙት ፓርቲ ነው።

ኢህአዴግ ግን አዲሲቷን ኢትዮጵያ የፈጠረና በአዲሰቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በተግባር ተፈትኖ ውጤት ያስገኘ ህዝባዊ ፓርቲ ነው። ኢህአዴግ በመጪው ምርጫ ላይ ይዟቸው የሚቀርቡ ለቁጥር የሚያታክቱ በተጨባጭ ተሞክረው ሃገሪቱን ማሳደግ፣ የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል፣ ሰላምን ማረጋገጥ . . . የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ባለቤት ነው።

ኢህአዴግ ገና የሚጠና ፓርቲ አይደለም። በተግባር የታየ ፓርቲ ነው። ከአመሰራረቱም በኢትዮጵያ የብሄር፣ ብሄረሰቦች መብትና ነፃነት መከበርን ዋናው ዓላማው አድርጎ የታገለና ያታገለ፣ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት በሕገመንግስት እንዲረጋገጥ በማደረግ ሂደት ውስጥ የጎላ ድርሻ ያለው፣ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብቶቻቸውንና ነፃነታቸውን በተጨባጭ እንዲያጣጥሙ ማድረግ የቻለ ፓርቲ ነው።

ኢህአዴግ ባለፉት አስራ ሁለት አመታት ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዘገብ የህዝቡን ኑሮ ማሻሻልና የሃገሪቱን ገፅታ መገንባት የቻለ ፓርቲ ነው። በቀደሙት ስርአቶች አፈር ግጦ የነበረውን የሃገሪቱን ገፅታ መልሶ መገንባት ችሏል። ይህ ዓለም የመሰከረለት እውነት ነው። ኢትዮጵያ አሁን በረሃብ፣ በድህነትና በጦርነት ምሳሌነት ሳይሆን ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ያስቻለ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ በዓለም ላይ የምትጠቀስ ሃገር ለመሆን በቅታለች። በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ተሞክሮዋን ለሌሎች ሃገራት እንድታቀርብ የሚቀርብላት ግብዣ ለዚህ አስረጂነት ሊጠቀስ ይችላል።

ኢትዮጵያ በእናቶችና በሕፃናት ሞት፣ በምግብ ራስን በመቻል ከግዜው አስቀድሞ የተባበሩት መንግስታትን የሚሊኒየም የልማት እቅድ በማሳካት እውቅና የተሰጣት ሀገር ለመሆን በቅታለች። ከ50 በመቶ በላይ የነበረውን የድህነት መጠን በግማሽ ገደማ መቀነስ ችላለች።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ በራስዋ አቅም የገነባቻቻው የተከዜ እና የጣና በለስ የሃይል ማመንጫዎች ኢትዮጵያ የደረሰችበትን ደረጃ ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ በብድር በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ በመገንባት ላይ ያሉት አስር ያህል የስኳር ፋብሪካዎች፣ ግዙፍ የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ በተለያዩ አካባቢዎች በመገንባት ላይ ያሉ የውሃና የንፋስ የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች፣ በቅርቡ የሚጠናቀቀው የአዲስ አበባን ጨምሮ በተለያየ አካባቢ በመከናወን ላይ የሚገኘው በሺሆች ኪሎሜትሮች የሚለካ የባቡር መስመር ግንባታ፣ በመላው ሃገሪቱ የተገነቡና በመገንባት ላይ የሚገኙ የመንገድ መሰረተ ልማቶች በሙሉ የኢህአዴግ ፖሊሲ ውጤቶች ናቸው።

ኢህአዴግ ልማታዊ መንግስት ነው። ኢህአዴገ የሚከተለወ ልማታዊ ፖሊሲ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በጥቂት ባለሃብቶች ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ሕዝብ ባሳተፈና ተጠቃሚ ማድረግ በሚችል ልማት ነው ኢኮኖሚውን የሚያሳድገው። ልማታዊ ፖሊሲው ከእያንዳንዱ ዜጋ ጋር - በገጠር ከእያንዳንዳንዱ አርሶ አደር ጋር፣ በከተማ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ከተደራጁ በብዙ ሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎች ጋር እንዲሁም ከልማታዊ ባለሃብቶች ጋር የቤተሰብ ያህል በመቀራረብና በመተሳሰር ተግባራዊ የሚደረግ ነው። በመሆኑም ህዝቡ ኢህአዴግን የቤተሰቡን አባል፣ የጎሬቤቱን ያህል ያውቀዋል። እናም የእወቁኝ ብዙ ቅስቀሳ ሳያስፈልገው "የጀመርኩትን ክህዝብ ጋር ሆኜ አስፈፅማለሁ" በማለት ብቻ የህዝብን ድምፅ ማግኘት የሚችል ፓርቲ ነው።

በመሆኑም ሞቶ የበሰበሰ አመለካከት ላይ ተቸንክሮ የቀረው አንድነት ሊፎካከረው አይችልም። በዚህ ላይ አንዳንድ የአንድነት አመራሮች የሻአቢያ ተላላኪ ከሆኑ በውጭ የሚኖሩ ቡድኖች ጋር ግንኙነት በመመሰረት ስለሚታወቁ፣ ፓርቲው ኢህአዴግ ላይ ቅሬታ ባላቸው ሰዎች ጭምር ድጋፍ እንዲያጣ አድርጎታል።

በአጠቃላይ አንድነት በአዲሲቱ ኢትዮጵያና በመጪወ ምርጫ ላይ ስፍራ እነዲኖረው ከፈለገ፣ የሃገሪቱን ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴና ዴሞክራሲ ማጎልበት ከፈለገ በቅደሚያ የውስጥ ችግሮቹን መፍታት ይጠበቅበታል። በመቀጠል በእርግጥ በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የህዝብ የስልጣን ውክልና ማግኘት ከፈለገ አቋሙንና ፖሊሲዎቹን ከአዲሲቱ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣም ይገባዋል።

ከዚህ ውጭ በሻአቢያ ተላላኪ ሚዲያዎች አጎብጋቢነት፣ ወደስልጣን መምጣት የሚያስችል መንገድ ይፈጠራል በሚል ግምት፣ እንዲሁም ውጭ ሃገር ያሉ ሌሎች ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የሚልኩትን ገንዘብ በመጎምጀት  በፉከራ በታጀቡ መግለጫዎች ጋጋታ ማቅራራቱ  የትም እንደማያደርስ ተረድቶ ቢቃና ጥሩ ነው። አለበለዚያ የተመሰረተበት ሙት አመለካከቱና የአመራሮቹ ውዝግብ ይዞት ገደል መግባቱ አይቀሬ ነው።